Home

# በ1997 ዓ.ም በሚካሄደው ብሔራዊ ምርጫ

# ከሲቪል ማኅበራት ምን ይጠበቃል?



*በአድማሱ ገበየሁ*[1]

## *መግቢያ*

በአሁኑ ጊዜ የአገራችን ሲቪል ማኅበራት[2] በብዛታቸውም በብቃታቸውም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ የአብዛኛዎቹ ሲቪል ማኅበራት ተሳትፎ በማኅበራዊ አገልግሎትና በቁሳዊ ልማት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሕዝባዊ ተሳትፎን ለማሳደግና መንግሥታዊ ተጠያቂነትን ለማምጣት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው:: በመብት መከበር፣ በሕግ የበላይነት መስፈን፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባትና በመልካም አስተዳደር መስፈን ተግባራዊነት ላይ ትኩረት ሰጥተው የሚንቀሳቀሱ በጣም ጥቂት ናቸው::ይሁን እንጂ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት የሲቪል ማኅበራት ደግሞ በዚህ አቅጣጫ አርአያ የሚሆን ሥራ በማከናወን ላይ መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል:: ከነዚህ አንዳንዶቹ ለመብት መከበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈን፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያላሳለሰ ትግል ሲያደርጉ፣ ሌሎች ደግሞ ሕዝባዊ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት የመንግሥት ፖሊሲዎችን በመገምገምና በመተቸት ገንቢ አስተያየትና ሃሳብ በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው::

ለአገራችን የድህነት መባባስ ዋነኛው ምንጬ መልካም አስተዳደርን ሊያስገኝ የሚችል የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር አለመቻሉ ነው:: ስለሆነም በአገራችን ሕዝባዊ ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ፖለቲካዊ ሥርዓት መመሥረት ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ የድህነት መቀነሻ ቁልፍ መፍትሄ ነው:: የፖለቲካው ችግር ባግባቡ ከልተፈታና ሁሉም ዜጎች በአገራችን ጉዳይ ካልተሳተፉ ድህነትን መቀነስ አይቻልም:: በመሆኑም የሲቪል ማኅበራት የዜጎችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ በኩል ብዙ ይጠበቅባቸዋል:: የዜጎችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ደህንነትን የሚያቃውሱ ድርጊቶች በዜጎች ላይ እንዳይፈፅሙ መከታተልና መከላከል የሲቪል ማኅበራት ሙሉ ዓላማቸው ወይም ከፊል ዓላማቸው አድርገው ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው:: በዚህ በኩል የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ ማድረግ ይችሉ ዘንድ እርስ በርሳቸው የአጋርነትን መንፈስ መፍጠር አለባቸው:: የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለማስፈንና ለማጎልበት ጠንካራ የሲቪል ማኅበራት መኖር አስፈላጊ ነው:: በተለይም በቅርብ ጊዜ የሚካሄደው የ1997 ዓ.ም ብሔራዊ

---

[1] ይህ ጽሑፍ የ1997 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫን አስመልክቶ የኢዴፓ የምርጫ ግብረ ኃይል የቅስቀሳና ማስታወቂያ ኮሚቴ ያዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ የካቲት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በዶ/ር አድማሱ ገበየሁ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው::

[2] መንግሥታዊ ያልሆኑ የእርዳታና የልማት ድርጅቶች፣ የአካባቢ ልማት ማኅበራት፣ የሙያ ማኅበራት፣ የብዙሃን ማኅበራት (የሠራተኞች፣ የገበሬዎች፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ ወዘተ)፣ የሃይማኖት ድርጅቶችና ሌሎች የአባሎቻቸውንም ሆነ የሌላውን ኅብረተሰብ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚንቀሳቀሱ ሁሉ የሲቪል ማኅበራት ሊባሉ ይችላሉ:: የሲቪል ማኅበራት ሊባሉ የሚችሉት የተጠቀሱት ብቻ እንዳልሆኑና ሌሎችም እንዳሉ ግልፅ ነው::

ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ እንዲሆን የማህበራቱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ በተጠናከረ መንፈስ መንቀሳቀስ ወሳኝነት አለው::

ከዚህ በማስከተልም በ1997 ዓ.ም በሚደረገው ብሔራዊ ምርጫ የሲቪል ማኅበራት ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ የታየኝን በስድስት ክፍሎች ከፋፍዬ ለማሳየት እሞክራለሁ:: እነዚህም: (1) የምርጫ ሕጉ እንዲሻሻል አስተዋጽኦ ማድረግ፣ (2) ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲቋቋም ጥረት ማድረግ፣ (3) የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ሚዛናዊ እንዲሆን አስተዋጽኦ ማድረግ፣ (4) የመራጮች የሲቪክ ትምህርት እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ማድረግ፣ (5) በታዛቢነት መሳተፍ፣ እና (6) ለምርጫው የሚበጅ ገንዘብ ማፈላለግ የሚሉ ናቸው::

## 1. የምርጫ ሕጉ እንዲሻሻል አስተዋጽኦ ማድረግ

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የምርጫ ችግሮች እርስ በርስ የሚደጋገፉና የተቆላለፉ ናቸው:: የአንዳንድ የምርጫ ችግሮች መነሻቸው አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት ነው:: ስለሆነም የኢትዮጵያን የምርጫ ችግሮች ለመፍታት ሲታሰብ የመጀመሪያው አማራጭ ሆኖ መቅረብ የሚገባው ሃሳብ ሕገ-መንግሥቱ መሻሻል አለበት የሚለው ነው::

አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት እንደሚመረጡና የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አናሣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እንደሚሆኑ ተገልጿል:: ይኸ ድንጋጌ የሚያሳየው በተወካዮች ምክር ቤት ደረጃ ለሚደረገው ምርጫ ሥራ ላይ የሚውለው አብላጫ ድምጽ ሥርዓት መሆኑን ነው:: ይሁን እንጂ የአብላጫ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት በርካታ ቅሬታ የሚቀርብበትና አከራካሪነቱ እየጨመረ የመጣ የምርጫ ሥርዓት ዓይነት ነው: ከሚቀርቡት ቅሬታዎችና ከሚነሱ ክርክሮች መካከል፣ አንደኛ በፓርላማ ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶችን፣ የሕዝቡን ማኅበራዊ ጥንቅርና መልክዓ ምድራዊ ውክልና በሚገባ ለማንፀባረቅ አያስችልም የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አሸናፊው የሚለየው የአብዛኛ ድምጽ ማግኘቱ ሳይረጋገጥ በድምጽ ብልጫ ብቻ በመሆኑ የሚመሠረተው መንግሥት ሠፊ የሕዝብ ድጋፍ የሌለው መንግሥት ይሆናል የሚል ነው::

የ«አብላጫ ድምፅ» ሥርዓት ለበርካታ ዓመታት ዴሞክራሲያዊ ባህል የገነቡና ተመጣጣኝ ጥንካሬ ያላቸው ፓርቲዎች ባሉባቸው አገሮች ተቃውሞ ላይገጥመው ይችላል:: ገና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በጅምር ላይ ላሉና የተለያዩ ማኅበረሰቦች ተሰባጥረው በሚኖሩበት አገር ግን ተመራጭ የምርጫ ሥርዓት አይደለም::

በሌላ በኩል ደግሞ ከአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የተለየዉ «ተመጣጣኝ ውክልና» የምርጫ ሥርዓት ለማንኛውም አገር ተስማሚ መሆኑ በበርካታ ተመራማሪዎች ተመስክሮለታል:: ይህ የምርጫ ሥርዓት በስዊዘርላንድ፣ በስፔይን፣ በፓርቱጋል፣ በሆላንድ፣ በስዊድን፣ በዴንማርክ፣ በኖርዌይ፣ በፊንላንድ፣ በአይስላንድ፣ በጀርመን፣ በኦስትሪያ፣ በሉክሰምበርግ፣ በጣሊያን፣ በግሪክ፣ በኔዘርላንድ፣ በቤልጅየም፣ በእስራኤል፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በናሚቢያና በሌሎች በርካታ አገሮች በተሳካ ሁኔታ ይሠራበታል:: ይህ «ተመጣጣኝ ውክልና» የምርጫ ሥርዓት የመራጮችን ድምፅ የማያባክን፣ ዴሞክራሲያዊ ውክልናን የሚያጠናክር፣ የደካማ ፓርቲዎችን መብት የሚያስጠብቅና በመንግሥት አመራርና አሠራር ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው::

ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የበለጠ የሚጠቅመዉ «ተመጣጣኝ ውክልና» የሚባለው የምርጫ ሥርዓት እንደሆነ ይታመናል:: ተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት በሁሉም መመዘኛዎች ተቀባይነት ያለው ተመጣጣኝ ውክልና በሚገባ የሚነፀባረቅባቸው ምክር ቤቶችን ለማቋቋም ከሚሰጠው ጥቅም ሌላ አንድ ዓይነት ሥርዓት በመላ አገሪቱና በየትኛ

ውም ደረጃ መዘርጋት ያስችላል:: ለፌደራል ምክር ቤት አንድ ዓይነት ሥርዓት ለክልል ምክር ቤቶችና ለወረዳ ምክር ቤቶች ደግሞ ሌላ ዓይነት የምርጫ ሥርዓት በመጠቀም የሚከሰተውን የሀብት (የሪሶርስ) መባከንና የአሠራር መዘባረቅ ያስወግዳል::

በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በክልሎችና በአካባቢ ደረጃ የሚመሠረቱ ምክር ቤቶች አባላት አመራረጥ ሥርዓት ምን እንደሆነ በግልፅ ባለመደንገጉ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ለማሸነፍ ይጠቅመኛል የሚለውን የምርጫ ስርዓት እንደፈለገው እየለዋወጠ እንዲጠቀም ልዩ ዕድል ሰጥቶታል:: የምርጫ ሥርዓቱን ሲቀያይር በምርጫው ለመወዳደር በሕግ የተመዘገቡትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳያማክር በድንገት ስለሚሆን ዝግጅታቸውንና ድካማቸውን ሁሉ ባልተጠበቀ ሁኔታ መና የሚያስቀርበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: በዚህ ድብቅ ሥልት እየተጠቀመ በክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች ደረጃ የሚኖሩትን ውክልናዎች ተገቢ ባልሆነ መንገድ ይቆጣጠራል::

የምርጫ ሥርዓት ችግሮች በሚነሱበት ጊዜ መታለፍ የማይገባው አንድ ነጥብ ቢኖር በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ነው:: ይህ ድንጋጌ «የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትን፣ በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሠጣቸው አናሣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ከ550 የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሣ ብሔረሰቦች ከ20 የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይደነገጋል::» ይላል:: ይኸንኑ ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 ግን እንዳንዱ የምርጫ ክልል 100 ሺህ ሕዝብ እንደሚያቅፍ ያሳያል::

የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር በዓመት 3 በመቶ ገደማ በሆነ ፍጥነት እያደገ የሚሄድ መሆኑ የታወቀ ነው:: በ1987 ዓ.ም የምርጫ አዋጁ በወጣበት ዘመን የሕዝቡ ቁጥር 55 ሚሊዮን ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ደግሞ 70 ሚሊዮን ደርሷል:: በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ 72 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል:: በምርጫ አዋጁ መሠረት ከተሰላ 720 የተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው:: ይህስ በሕገ-መንግሥቱ ከተደነገገው «ከ550 የማይበልጥ» ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል? ሁለቱ ሊስማሙ የቻሉት ለዚያው ለ1987 ምርጫ ብቻ ነው:: ከዚያ ወዲህ ላሉት ሁኔታዎች እንዲሠራ ለማድረግ ከተፈለገ የምርጫ ሕጉ እንደገና መስተካከል አለበት::

ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 38 መምረጥና የመመረጥ መብትን አስመልክቶ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመመረጥ መብት እንዳለው ደንግጓል:: የምርጫ ሕጉ (አዋጅ ቁጥር 111/1987 ዓ.ም) ግን በአንቀጽ 38 ማንኛውም ኢትዮጵዊ የዕጩነትነትን መመዘኛ ለማሟላት የሚወዳደርበትን የብሔራዊ ክልል ቋንቋ የማወቅ ግደታ እንዳለበት አስፍሯል:: በሕገ-መንግሥቱ ሳይሸራረፍ እውቅና ያገኘን መብት የምርጫ አዋጁ ጥሶታል::

ምንም እንኳን እጅግ አሳሳቢ ቢሆኑም በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ለሌላ ጊዜ መተላለፍ ይኖርባቸውል የሚል እምነት አለኝ:: ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ሂደት ተጀምሮ ለማጠናቀቅ እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ የሚበቃ አይመስለኝም:: ሆኖም ከሕገ-መንግሥቱ በመለስ ያለውን የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/87 ማሻሻል ግን ይዋል ይደር የሚባል ጉዳይ አይደለም:: ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች የምርጫ ሕጉ ችግር እንዳለበት ለማመላከት ያህል ብቻ የቀረቡ ናቸው:: ሆኖም እጅግ በርካታ መሰናክሎችን የፈጠረና በርካታ ችግሮችን መፍታት ያቃተው አዋጅ መሆኑን የሚያሳዩ በተለያዩ ወገኖች የቀረቡ በቂ መረጃዎች አሉ::

ሲቪል ማኅበራት ከምሁራንና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመሆን የምርጫ ሕጉን በመከለስ የማሻሻያ ሃሳቦችን ቢያቀርቡ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚኖረው አያጠራጥርም:: ለመነሻ የሚሆኑ ሰነዶች ከሁን ቀደም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) «የምርጫ ሕጉና ችግሮቹ» በሚል ርዕስ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲወያዩበት አቅርቦት የነበረው ሰነድ፣

በተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተዘጋጁ ሰነዶች፣ በቅርብ ጊዜ በ«ልሳነ ሕዝብ» ጋዜጣ በተከታታይ «የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ቅኝት»[3] በሚል ርዕስ የቀረቡ ጽሑፎች ለመነሻነት ሊያገለግሉ ይችላሉ:: እነዚህ በተለያዩ ወገኖች የቀረቡት ሰነዶች በበርካታ ነጥቦች ላይ ተመሳሳይነት አላቸው:: በመሆኑም ለማዛመድ፣ ለማዋሃድና ለማጠቃለል የሚያስፈልገው ሥራ ቀላል ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል «ተመጣጣኝ ውክልና» የምርጫ ሥርዓት ለአገራችን ሁኔታ ተመራጭ መሆኑን ሁሉም ሰነዶች የሚጋሩት ነጥብ ነው:: ይህ ሥርዓት በሚቀጥለው ምርጫ የክልል ምክር ቤት አባላትን ለመምረጥ እንደሚያገለግል ሆኖ በሕግ ተደንግጎ ሊወጣ ይችላል::

## 2. ነፃና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ እንዲቋቋም ጥረት ማድረግ

አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት የመንግሥት ሥልጣን በአስፈፃሚው ሥር በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ውስጥ ተጠቃሎ እንዲገባ መፍቀዱ ያስከተለው ሌላው ችግር የአገሪቱ ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ሊቋቋምና ሊሠራ እንዲችል ያለማድረጉ ነው::

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሂድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል የሚል ተደንግጓል:: በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፤ ይላል:: ይኸንኑ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ጋር ለማጣጣም አዋጅ ቁጥር 111/1987 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል:: በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የምርጫ ቦርዱን ዋና ኃላፊና ምክትል ዋና ኃላፊ መርጠው በተወካዮች ምክር ቤት የሚያሾሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ናቸው::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ምርጫ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤቶችን የሚመሩ ኃላፊዎች ከብሔራዊ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት ጀምሮ እስከ ምርጫ ጣቢያ ድረስ ያሉት ሙሉ በሙሉ አሁን ሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ እየተመለመሉ የሚመደቡ ናቸው:: የምርጫ ወረቀትና ልዩ ልዩ ቁሳቁስ የሚገዙ፣ የሚያከማቹ፣ የሚያሳትሙ፣ የሚያሰራጩና የሚቆጣጠሩ እነዚህ በምርጫ አስፈጻሚነት ስም በአንድ ፓርቲ ተመልምለውና ሠልጥነው የተመደቡ ሰዎች ናቸው:: ድምፅ የሚቆጥሩና የምርጫ ውጤት ሪፖርት የሚያዘጋጁ እነዚሁ ሰዎች ስለሆኑ፣ የፈለጉትን አላፊ፣ ያልፈለጉትን ወዳቂ ከማድረግ የሚያግዳቸው ነገር የለም::

ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የማይወግን የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም በአገሪቱ ካልተፈጠረ የመንግሥት ሥልጣን የያዘ ፓርቲ ባርኔጣውን እየቀያየረ ሲፈልግ መንግሥት፣ ሲፈልግ ፓርቲ፣ ሲፈልግ የምርጫ ቦርድ፣ ሲፈልግ ደግሞ ምርጫ አስፈፃሚ በመሆን ሥልጣኑን ሲያራዝም ይኖራል እንጂ ነፃ ምርጫና በዚህ ላይ ተመሥርቶ የሚገነባ የዴሞክራሲ መንግሥት መፍጠር አይቻልም:: ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲኖር ከተፈለገ የተሻለው የመፍትሔ አማራጭ የምርጫ ቦርዱና አስፈፃሚ አካላቱ በመንግሥት አስፈፃሚው አካል ተፅዕኖ ሥር ከወደቁበት አደረጃጀት እንዲላቀቁ ማድረግ ነው::

ከላይ እንደጠቆምኩት፣ ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ሂደት ተጀምሮ ለማጠናቀቅ እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ የሚበቃ አይመስለኝም:: ሆኖም በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገው ሳይቀየር ምርጫ ቦርድን አሁን ካለው በተሻለ ሁኔታ ማቋቋምና ማደራጀት እንደሚቻል

---

[3] ይህንን ጽሑፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉመው ያቀረቡት አቶ ደርበው ተመስገን ሲሆኑ የእንግሊዝኛው ጽሑፍ በማን እንደተዘጋጀ እንደማይታወቅ ከቀረቡት ጽሑፎች ላይ ተጠቁሟል::

ይታየኛል:: የምርጫ ቦርዱ አባሎች ከሲቪል ማኅበራት መሪዎችና ከታዋቂ ግለሰቦች የተውጣጡ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚቻልና ይህንንም ሠፊ ውይይት በሚያስተናግድ መድረክ መፍጠር እንደሚቻል ይታየኛል:: ይህም ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲቀበሉት ሲቪል ማኅበራት አስፈላጊውን ሁሉ ግፊትና ጫና የመፍጠር እንቅስቃሴ ይጠበቅባቸዋል::

## 3. የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ሚዛናዊ እንዲሆን አስተዋጽኦ ማድረግ

የመገናገኛ ብዙኃን በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚኖራቸዉ ሚና እጅግ የላቀ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ባሁኑ ሥርዓት በአደረጃጀት ችግር ተጠልፎ የወደቀ የሕዝብ ተቋም ነው:: ይህ ተቋም ሚዛናዊ የሆነ መረጃ እየሰበሰበ በማሰራጨትና በማሳወቅ መራጩን ሕዝብና በምርጫ የሚወዳደሩትን የተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች በእኩልነት እንዳያገለግል ተደርጎ በሚያሳዝን መንገድ የአንድ ቡድን የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የተደራጀ ነው:: የመንግሥት ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሬስ ድርጅቶች በወያኔ/ኢሕአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች አመራር ሥር እንዲወድቁ ሆነዋል:: ነፃ አደረጃጀትና አሠራር እንዲኖቸው በቦርድ የሚተዳደሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ነበር:: ነገር ግን ኢሕአዴግ መሪ ካድሬዎቹን በእነዚህ ተቋሞች የቦርድ ኃላፊነትና አባልነት በመመደብ የታሰበው ነፃ አደረጃጀትና አሠራር በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም:: በዚህም ምክኒያት የመገናኛ ብዙሃን የገዢው ፓርቲ አወዳሽ ሆነው እንዲሠሩ ተገደዋል:: በምርጫ ጊዜ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን አቋም በማንቋሸሽ ከሚሠሩት አስነዋሪ ተግባር በተጨማሪ መግለጫዎቻቸውንና ማስታወቂያዎቻቸውን እየቆራረጡና እያዛቡ ሲያሰራጩ ታይተዋል::

የመንግሥት ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሬስ ድርጅቶች የአንድ ፖለቲካ ድርጅት የግል ንብረት እስኪመስሉ ድረስ ግብር እየከፈለ ያቋቋማቸውን መራጩን ማገልገል እንደተሳናቸው ለመታዘብ ተችሏል:: የእነዚህን የሕዝብ ተቋማት ተልዕኮ የጠለፈውና ለራሱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ አድርጎ መጠቀምን የመረጠው ገዢው ፓርቲ ይኸንን ሲያደርግ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና ፕሬስ እጥረት ስላጋጠመው አይደለም:: ሌላ ተሻሚ የማይቀርብባቸውና የግሉ ንብረት እንደሆኑ የሚታወቁ ነገር ግን ሕግ ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጭ ያቋቋማቸው የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች አሉት:: ዜና በማሰባሰብና በማሰራጨት ተግባር ተሠማርተው እንደፈለጋቸው የሚሠሩ እንደ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልና እንደፋና ሬዲዮ ያሉ ተቋሞች አሉት:: ሥርጭታቸው በአንዳንድ ክልሎች የተወሰኑ የድርጅቱ ሬዲዮ አገልግሎት መስጫ ተቋሞችም አሉት:: እነዚህ ከገዢው ፓርቲ ሌላ ለማንም አገልግሎት እንዲሰጡ ጥያቄ የሚቀርብላቸው አይደሉም:: የተቋቋሙበት አግባብ ሕገወጥ ቢሆንም ባለንብረቱ ኢሕአዴግ ራሱ መንግሥት እንደመሆኑ ለመጠየቅና ለመክሰስ የሚችል አንድም ኃይል ስለሌላ የፕሮፓጋንዳና የሚዲያ ንግድ ሞኖፖል ፈጥረው እንዳሻቸው ይሠራሉ:: በምርጫ ጊዜ ሙሉ ኃይላቸውን እየተጠቀሙ በኢሕአዴግ ተቃዋሚዎች ላይ ያነጣጠረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ይከፍታሉ:: ድርጅቶችን የሚያጥላላ ብቻ ሳይሆን በድርጅቶቹ ውስጥ የገቡትን ግለሰቦች ስብዕና የሚነካ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሂዳሉ::

የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በሕዝብ ሃብት የሚተዳደሩ የሕዝብ ንብረት እንደመሆናቸው አንድ ሥልጣን የያዘ ፓርቲ በብቸኝነት ሊመራቸው፣ ሊቆጣጠራቸውና ሊገለገልባቸው አይገባም:: የሕዝቡ ዐይንና ጆሮ ሆነው መሥራት እንዲችሉ በመገናኛ ብዙሃን አመራር ቁጥጥርና አሠራር ሕዝቡ ተሣትፎ የሚያደርግበት ሁኔታ መፈጠር አለበት::

ሕዝቡ ከአንድ ፓርቲና መንግሥት የሚመነጭ ሃሳብና አስተያየት ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ፓርቲዎች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚመጡ ልዩ ልዩ አመለካቶችን በመገናኛ ብዙሃን ማድመጥ ይፈልጋል:: ከተለያዩ ምንጮች የሚቀዱ ዜናዎችና መረጃዎችን ማግኘት መብቱ ነው:: ዕውነት ከአንድ ወገን ብቻ የሚገኝ ባለመሆኑ ከተለያዩ ምንጮች ሚዛናዊ መረጃዎችን እየሰበሰቡ ለሕዝቡ ማሳወቅ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ግዴታ ነው:: ሕዝቡ ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብቱንና የመገናኛ ብዙሃን ደግሞ ይኸንኑ ሚዛናዊ መረጃ ለሕዝቡ የማሰራጨት

ግዴታቸውን እንዲወጡ በአደረጃጀታቸውና አሠራራቸው ሕዝቡ ሙሉ ተሣትፎ ማድረግ መቻል አለበት:: ሕዝቡ ለእነዚህ ተቋሞች ሕልውና የሚያገለግል መዋጮና ግብር የመክፈል ግዴታ ብቻ ሳይሆን የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ በአመራር ተሣትፎ በማድረግ፣ አሠራራቸውን በመቆጣጠር፣ በመተቸትና በማረም ሠፊ አስተዋፅኦ የማድረግ መብት አለው:: ሕዝቡ ይኽንን መብቱን ለመጠቀም እንዲችል የመገናኛ ብዙሃኖችን የሚመሩት ቦርዶችና ልዩ ልዩ አካላት ሲዋቀሩ ከአንድ ፓርቲ አባላት በሚወከሉ ሰዎች ብቻ መሆን አይገባውም:: የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ተቋሞች፣የተለያዩ ሞያተኞችና ታዋቂ ዜጎች በቦርድ አባልነትና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አመራር ሥራ ውስጥ ተሣትፎ ማድረግ አለባቸው::

በዚህ መልኩ የሚቋቋም ቦርድ የመግሥት መገናኛ ብዙሃንን ብቻ ሳይሆን የግል ፕሬስን ጭምር የሚከታተል ቢሆን ይመረጣል:: የመንግሥትም ሆነ የግል መገናኛ ብዙሃን ሕዝቡን የማገልገል ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና በእነዚህ ዘርፎች የተሠማሩ ሞያተኞችም የሞያውን ሥነምግባር ጠብቀው እንዲሠሩ ኮሚቴው ትልቅ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ ለተቃዋሚዎች ጭምር በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን የመጠቀም እኩል ዕድል ሊሰጥ ይችላል::

## 4. የመራጮች የሲቪክ ትምህርት እንዲስፋፋ አስተዋጽኦ ማድረግ

በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲኖር ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል የሲቪክ ትምህርት አንደኛውና ዋነኛው ነው:: በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ምርምር ሥራ የተሠለፉትን ተቋሞች ነፃ አድርጎ ማደራጀት፣ የሞያተኛና የቴክኒክ አቋማቸውን ማሟላት፣ የፋይናንስ ምንጫቸውን ማስፋትና አሠራራቸውን ሁሉ ዘመናዊ ማድረግ የሥርዓተ-ትምህርቱ አዘገጃጀት ጥራት፣ በይዘቱ ሙሉነትና በዓላማው ስፋት ላይ የሚኖራቸው አስተዋጾ ከፍተኛ በመሆኑ ለእነዚህ ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው:: እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎች በማሟላት ዜጎችን በሲቪክ ትምህርት መኮትኮት ለነፃ ምርጫና በዚህ ላይ ተመሥርቶ ለሚገነባ የዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር ወሣኝ አስተዋፅዖ አለው:: የነፃ ምርጫና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች በምርጫ ዋዜማ ተጀምረው ከምርጫ ውድድር መጠናቀቅ በኋላ የሚቆሙ የአንድ ሰሞን ሥራዎች አይደሉም:: ዘላቂነትና ተከታታይነት በሌለው መንገድ ተጀምረው የሚቋጩም የዘመቻ ሥራዎች አይደሉም:: ጥልቀት ባለው ምርምርና ጥናት ሠፊ ራዕይና የተሟላ ይዘት ባለው ሥርዓተ ትምህርት ላይ በሚመሠረት ተከታታይ የሲቪክ ትምህርት እየታገዙ በተቀናጀ የዜጎች ነፃ ተሣትፎና በሂደት የሚሳኩ ናቸው:: ስለዚህ ለነፃና ዴሞክራሲያዊ መርጫ ሲታሠብ የዜጎች የተሟላ ንቁ ተሣትፎ ስለሚፈጥረው የሲቪክ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሠጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው::

ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ ግንዛቤ እንዳለ ሆኖ በአጭር ጊዜ በተለይም በ1997 ዓ.ም ምርጫ ምን መደረግ አለበት የሚለውን ለመጠቆም እፈልጋለሁ:: የሲቪክ ትምህርት በምርጫ ዋዜማ በመገናኛ ብዙሃን፣ በሲምፖዚየም፣ በፖለቲካ ድርጅቶች የክርክር መድረኮች፣ በስብሰባ አዳራሽ፣ በአደባባይ መግለጫዎች በሚደረግ ጥረት ብቻ የተወሠነ መሆን አይገባውም:: የመገናኛ ብዙሃን፣ የምርጫ ተቋሞች፣ የሲቪል ማህበራት ከወዲሁ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ መድረኮች በመፍጠር የሲቪክ ትምህርት እንዲስፋፋ በርትተው ቢሠሩ ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል የበርካታ አገሮች ልምድ ያሳያል::

በ1992 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)፣ የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤቶች («ምረጥ አዲስ» እና «ይቻላል» በሚል መሪ መፈክር በመመራት)፣ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ፣ እና ሌሎችም የውይይት መድረክ በመፍጠር ያደረጉት አስዋጽኦ ጥሩ ጅማሬ ነው:: ወደፊትም እንደዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ በዓይነትም በስፋትም በተጠናከረ መልኩ መቀጠሉ አስፈላጊ ነው::

## 5. በታዘቢነት መሳተፍ

ምርጫን በተመለከተ ጎልተው ከሚታዩት ችግሮች መካከል ምርጫውን በሚታዘቡ የአገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች ላይ የሚደረገው ተፅዕኖ አንዱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለመኖሩ የምርጫውን ሂደት የሚታዘቡ አካላት ተሳትፎ እንዲኖርና እውነቱን ሕዝብ በይፋ እንዲያውቀው በማድረግ እገዛ እንዲያደርጉ በተቃዋሚ ፓርቲዎችም በሕዝብም በኩል ከፍተኛ ፍላጎት አለ፡፡ ዓለም-አቀፉ ሕብረተሰብም ታዛቢዎችን እየመደበ የኢትዮጵያ ምርጫ ሂደት እንዲከታተልና ለዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ጉጉት አለ፡፡ በዘመናችን አስተሳሰብ ዴሞክራሲን በአንድ አገር የመፍጠር ጥያቄ ዓለም-አቀፍ ትርጉም ያለውና የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ምክንያቱም የአንድ አገር ሕዝብ ዴሞክራሲ ሲያጣ የሚከተለው የሰላም መጥፋትና የልማት ዕድል መዘጋት ጉዳቱ በዚያ አገር ተወስኖ የሚቀር እንዳልሆነ የታመነበት በመሆኑ ነው፡፡ ችግሩ ለጎረቤት አገሮች፣ ለአህጉርና ለዓለም መትረፉ የማይቀር ነው፡፡ የዓለምን ሰላም፣ ደህንነትና ልማት የመንከባከብ ኃላፊነት ያለበት አለም አቀፉ ሕብረተሰብ በኢትዮጵያ ውስጥም ነፃና ትክክለኛ ምርጫ መካሄዱን መታዘብ ይኖርበታል፡፡ ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብና አገር በቀል የሲቪክ ማህበራት የዚህ ዓይነቱን ሚና በሌሎች አገሮች እንደሚጫወቱና ጠቃሚ ውጤትም እንዳስገኙ ይታወቃል፡፡

በ1992 ምርጫ ታዛቢነት በአገር ውስጥ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ) እና ጥቂት የሲቪል ማኅበራት ጥረት አድርገዋል፡፡ በተለይም ኢሰመጉ አቅሙ የፈቀደውን ያህል የምርጫውን ሂደት ተከታትሎ በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ያቀረበው ሪፖርት እጅግ የታመነና የተከበረ ነበር፡፡ ሆኖም በነበረበት የአቅም (በተለይም የገንዘብ አቅም) ማነስ ምክኒያት የሚፈልገውንና የሚፈለገውን ያክል በመላ አገሪቱ የተካሄደውን ምርጫ እንቅስቃሴ ሊሸፍን አልቻለም ነበር፡፡

በ1992 ምርጫ አገር ውስጥ ያሉት የውጭ ዲፕሎማቶች የተወሰነ ሙከራ ቢያደርጉም በአገሪቱ የመልክዓ ምድር ስፋትና በእነሱም በኩል ባለው የሰው ኃይል ውስንነት በሚፈለገው መጠን የአገሪቱን የምርጫ ሂደት ሙሉ በሙሉ ለመታዘብ አልቻሉም፡፡ የምርጫን ሂደት በመታዘብ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውና በሚያቀርቡት ትክክለኛ መረጃ ትልቅ ከበሬታ ያገኙ ተቋሞች፣ የመንግሥታት ተወካዮች፣ ዓለም-አቀፍ ድርጅቶች የሰው ልጅ መብት ተንከባካቢ አካላት፣ ፈቃደኛ ቡድኖችና ግለሰቦች ወደ አገር ወስጥ ገብተው ለመታዘብ ፍላጎት ቢያሳዩም ገዢው ፓርቲ እንዲገቡና እንዲታዘቡ ሊተባበር ባለመፈለጉ ምርጫው የተካሄደው ብቁ ታዛቢዎች በሌሉበት ሁኔታ ነበር፡፡

ባለፈው ምርጫ፣ ገዢው ፓርቲ ከየአቅጣጫው የሚደርስበትን ወቀሳ ለመከላከል ይረዱኛል የሚላቸውን ዘዴዎች ሁሉ ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ አንደኛው ዘዴ ሲቪል ማኅበራት እያስመሰለ ባደራጃቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱን ጥቅም እንዲያራምዱ ያቋቋማቸውን ድርጅቶች በነፃ ታዛቢነት ስም አሠማርቶ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ተካሂዷል የሚል የፈጠራ ሪፖርት በማዘጋጀት ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሰራጨት ሞክሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀጽ 23 በሕግ እውቅና ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተወካዮቻቸው አማካይነት የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ እንደሚችሉ የተደነገገ ቢሆንም ተግባር ላይ ሲውል ከፍተኛ ችግር ታይቷል፡፡ በተለይም የፖለቲካ ድርጅቶች በየምርጫ ጣቢያው የሚመድቧቸውን ታዛቢዎች ሕግ ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ በምርጫ ጣቢያ ተገኝተው እንዳይታዘቡ ተከልክለዋል፡፡ የምርጫውን ሂደት አውከዋል የሚል የፈጠራ ክስ እየተፈለገ ከመታዘብ ሥራቸው እንዲታገዱ ተደርጓል፡፡ ዛቻና ማስፈራራትም ተፈፅሞባቸዋል፡፡

ለመጭዉ ምርጫ በታዛቢዎች ላይ ባለፉት ምርጫዎች የታዩ ጉድለቶች በሙሉ እንዲታረሙ ሠፊ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። የሲቪል ማኅበራት ጥረትና ውጤት ምን እንዲሚመስል በተለይም የምርጫ ታዛቢነትን ሚና በተመለከተ የካምቦዲያንና የኬንያን ልምድ በምሳሌነት ማየት ይቻላል። በተለይም የካምቦዲያና የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክና ያሉበት የእድገት ደረጃ እጅግ ተመሳሳይ በመሆኑ ለየት ያለ ትኩረት መስጠቱ ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ፊውዳላዊ መንግሥት በመስከረም 1967 ዓ.ም በደርግ ሲገለበጥ በካምቦዲያ ደግሞ የሎን ኖል ፊውዳላዊ መንግሥት በሚያዚያ 1967 ዓ.ም በካመር-ሩዥ ተገለበጠ። በኢትዮጵያ የደርግ አገዛዝ እስከ ግንቦት 1983 ዓ.ም ድረስ ሲቆይ በካምቦዲያ ደግሞ መጀመሪያ የፖል ፖት በኋላም በቬየትናም በሚታገዝ ቡድን አገዛዞች አስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ቆይተዋል። በሁለቱም አገሮች ከ1967 አስከ 1983 ዓ.ም ድረስ የቆዩት አገዛዞች ሶሻሊስታዊ ፍልስፍናን መሠረት ያደረጉ ነበሩ። በኢትዮጵያ ከ1983 እስከ 1987 ድረስ የቆየ፣ በካምቦዲያ ደግሞ ከ1983 ዓ.ም አስከ 1985 ዓ.ም ድረስ የቆዩ የሽግግር አገዛዞች ተመሠረቱ። ከዚህ በኋላ በሁለቱ አገሮች አካሄድ ልዩነቶች እየተፈጠሩ መጡ። ካምቦዲያዊያን በ1985፣ 1990 እና 1995 ዓ.ም ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ማካሄድ ሲችሉ፣ እኛ ግን አስካሁን ድረስ ሊሳካልን አልቻለም። ካምቦዲያዊያን በ1995 ዓ.ም የምርጫ ሕጋቸውን አሻሽለዋል፣ እኛ ግን ገና አልሞከርነውም። ካምቦዲዊያንና እኛ በቅርብ ጊዜ የነበርንበት ሁኔታችን ይመሳሳል እንጂ አሁን የደረስንበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ግን በጣም ይራራቃል። አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ በተለይም በምርጫ ጊዜ የሲቪል ማኅበራት ያሳዩትን የምርጫ ታዛቢነት ተሳትፎ ለማሳየት በንፅፅር መልክ የቀረበውን መረጃ በሰንጠረዥ 1 ውስጥ መመልከት ይቻላል። በ1995 ዓ.ም በተደረገው የካምቦዲ ብሔራዊ ምርጫ የሲቪል ማኅበራት መድረክ 29637 የአገር-በቀል ታዛቢዎችን በማሰማራት ውጤታማ እንቅስቃሴ አድርጓል። በእኛስ አገር ይህንን አይነት እንቅስቃሴ በ1997 ዓ.ም ማድረግ እንችላለን? እራሳችንን እንጠይቅ!

እዚሁ ጎረቤታችን ኬንያ በ1989 ዓ.ም የኬኒያ ሲቪል ማኅበራት ከ28000 በላይ የሚሆኑ አገር-በቀል የምርጫ ታዛቢዎችን በማሰልጠን በ126000 የምርጫ ጣቢያዎች ማሰማራት ችለዋል። እነዚህ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት መከታተልና መገምገም ያስቻለ፣ ከዚያ በፊት በአፍሪቃ ምድር ያልታየ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እኛስ በሚቀጥለው በ1987 ዓ.ም ምርጫ ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ማስረግ ይሳነናል?

ከሁለቱም በምሳሌነት ከቀረቡት አገሮች የምንማረው ቁም ነገር ሲቪል ማኅበራት በቅንጅት መድረክ ፈጥረው ከተንቀሳቀሱ መተኪያ የሌለውን ሠፊ የምርጫ ታዛቢነት ሥራ በአግባቡ መሸፈን እንደሚችሉ ነው። ይህ ደግሞ ለምንፈልገው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

## 6. ለምርጫው የሚበጅ ገንዘብ ማፈላለግ

በምርጫ እንቅስቃሴ ላይ እኩል ዕድል እንዳይኖር መሰናክል ከሚሆኑት ዋናኛ ምክኒያቶች አንዱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለባቸው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ነው። መንግሥት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድጎማ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በሕግ የተደነገገ ቢሆንም እስካሁን ይህንን ኃላፊነቱን አልተወጣም። ተቃዋሚዎች ከማንኛውም የውጭ መንግሥት፣ ድርጅትና ዜጋ ማንኛውንም እርዳታ እንዳቀበሉ በሕግ ታግደዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ተቃዋሚዎችን በገንዘብ ረድቶ ማጠናከር ይቅርና ለራሱም ዳቦ ገዝቶ ለመብላት ተቸግሯል። ፓርቲዎችን ለመርዳት አቅም ያላቸው ጥቂት የሕብረተሰብ ከፍሎች ቢኖሩም የገዢውን ፓርቲ ተጽእኖ በመፍራት በሰቀቀን የሚኖሩ ናቸው። አንድ ፓርቲ ያለገንዘብ አቅም በከተሞቹም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ከፍቶ፣ ሕዝቡን በብቃት አደራጅቶና ቀስቅሶ በምርጫ ብቁ ተወዳዳሪ ሊሆን አይችልም። የንግድ ድርጅቶች ከፍቶ በብዙ ቢሊዮን ብር ካፒታል የሚነግድና የአገሪቱን ሁለንተናዊ ሀብት በብቸኝነት የተቆጣጠረ ኃይል አንድ

ብስክሌት ከሌላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በምርጫ እየተወዳደረ በዚህ አገር ነፃና ፍትሐዊ የምርጫ ሂደት ማየትም ሆነ ዴሞክራሲዊ ሥርዓትን መገንባት አይቻልም።

በተለያዩ አገሮች የምርጫ ውድድር ለሚያደርጉ እጩዎች የገንዘብ ድጎማ በመንግሥት በኩል መስጠት እየተለመደ መጥቷል። ይህ አሠራር በ1946 ዓ.ም በኮስታ ሪካ ተጀመረ። ከዚያም በአርጀንቲና፣ በጀርመን ቀጥሎ በእለፍ ተቀደም በአውስትሪያ፣ በፈረንሳይ፣ በስዊድን፣ በፊንላንድ፣ በደንማርክ፣ በእስራኤል፣ በኖርዌይ፣ በብራዚል፣ በሆላንድ፣ በካናዳ፣ በኢጣሊያ፣ በጃፓን፣ በአሜሪካ፣ በስፔይን፣ በሜክሲኮ፣ በቬንዙላ፣ በቱርክ፣ በአውስትራሊያና በሌሎችም በርካታ አገሮች በተግባር ላይ ውሏል። በእኛም አገር በዝርዝር ሕግ የሚመራ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈጠር ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪል ማኅበራት በጋራ ቢንቀሳቀሱ ውጤት መምጣት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

## ማጠቃለያ

በሚቀጥሉት ዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ መለወጥ አለበት። የአንድ ፓርቲ ሥርዓት ማክተም አለበት። እያንዳንዱ ዜጋ የሚሰጠው አንድ ድምፅ የተንሰራፋውን አገዛዝ ለመጣል ትልቅ ዋጋ እንዳለው አምኖ ነፃና ፍትሐዊ የምርጫ ሥርዓት እንዲፈጠር በሚደረገው ትግል ተሣትፎ ከማድረግ መቆጠብ የለበትም።:: ሕዝቡ ለዴሞክራሲ ኃይሎች የድጋፍ ድምፁን መስጠት ብቻ ሣይሆን በዴሞክራሲ ስም መብቱንና ነፃነቱን ለነጠቁት አምባገነኖች ደግሞ ድምፁን መንፈግ ከቻለ በእርግጥም የሕዝብ ትግል አሸናፊነት እንደማይቀር መተማመን ይቻላል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ነፃና ትክክለኛ የምርጫ ሥርዓት እንዲኖር ከተፈለገና በተለይም በ1997 ዓ.ም በአገራችን የሚካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ከአሁን በፊት ከተካሄዱት ምርጫዎች የተሻለ ውጤትና ትርጉም እንዲኖረው ያስፈልጋል። የምርጫው ዕለት ሲቃረብ ሳይሆን አሁኑኑ መጀመር ካለባቸው እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ዋናዋናዎቹ የምርጫውን ሕግ ማሻሻል፣ አዲስና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ማቋቋም፣ ተቃዋሚዎች በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዕድል ማመቻቸት፣ ተቃዋሚዎች የምርጫ ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችላቸው የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግና አገር-በቀልና ዓለም-አቀፍ የሲቪል ማህበራት የምርጫውን ሂደት ከወዲሁ ጀምሮ የሚከታተሉበት ሁኔታ መመቻቸት ብርቱ ትግል የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው። ሕዝቡ ለእነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ይገኝ ዘንድ ከወዲሁ ትግሉን በተጠናከረ ሁኔታ ማካሄድ ይጠበቅበታል። ለዚህ ሂደት መሳካት ደግሞ የሲቪል ማኅበራት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው።

ግልጽ የሆነ፣ ተጠያቂነት ያለበት ፓለቲካዊ ሂደት እንዲፈጠርና የዴሞክራሲ ባሕል በዜጎች እንዲለመድ የሲቪል ማኅበራት መድረክ መፈጠር ወሳኝነት አለው። እንደዚህ ያለው መድረክ የተሻሻለ የምርጫ ሕግ ረቂቅ ለማዘጋጀት፣ ለምርጫ የሚበጁ የማስተማሪያ የሚሆኑ ሰነዶችን ለማዘጋጀት፣ በቂ ታዛቢዎችን ለማሰልጠንና ለማሰማራት፣ የሕብረተሰቡን እንቅስቃሴ ለመምራት የሚችሉ በጎ ፈቃደኛ የሆኑ የተማሩ ዜጎችን ማሰባሰብ ስለሚችል አስተዋጽኦው የጎላ ነው። ሲቪል ማኅበራት የፖለቲካ ክርክርና ውይይት እንዲኖር ልዩ ልዩ መድረኮችን መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

በምርጫ ጊዜ በታዛቢነት መሠማራትና ያዩትን የታዘቡትን በሃቅ በይፋ በመመስከር የሕዝብ ፍላጎት በሚከበርበት ሥራ ላይ መሳተፍ የሲቪል ማኅበራት ሁሉ ግልፅ እተዋጽኦ ነው። ሆኖም መብትን፣ የሕግ የበላይነትንና የዴሞክራሲያዊ ሂደትን በተመለከተ በተሚጋችነትና በተጋፋጭነት ሚና የሚሰማሩ ገና ብዙ ሲቪል ማኅበራትና የተጠናከረ የጋራ መድረክ መፈጠር ይኖርበታል።

## ሰንጠረዥ 1፡ የኢትዮጵያና የካምቦዲያ የምርጫ ሁኔታ ሲነፃፀር

| ቁ | ክስተት/ሁኔታ | ኢትዮጵያ | ካምቦዲያ | ንጽጽር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የ1996 ዓ.ም የሕዝብ ብዛት (ሚሊዮን) | 70.0 | 13.4 | 5.2 |
| 2 | ዓመታዊ የሕዝብ እድገት (መቶኛ) | 2.8 | 2.4 | |
| 3 | በግብርና የተሰማራው የሰው ኃይል (መቶኛ) | 80 | 80 | |
| 4 | የአገር የቆዳ ስፋት (ሺ ስኩዌር ኪሎ ሜትር) | 1127 | 181 | 6.2 |
| 5 | የለም መሬት መጠን (መቶኛ) | 12 | 13 | |
| 6 | የፊውዳሊዝም ሥርዓት ያከተመበት ዘመን (ዓ.ም) | 1967 | 1967 | |
| 7 | የሶሻሊዝም ቅኝት ዘመን (ዓ.ም) | 1967-83 | 1967-83 | |
| 8 | የሽግግር ዘመን (ዓ.ም) | 1983-87 | 1983-85 | |
| 9 | ብሔራዊ ምርጫ የተከናወነበት ዘመን (ዓ.ም) | 1987፣ 1992 | 1985፣ 1989፣ 1995 | |
| 10 | የአስፈፃሚነት ሥልጣን ለመያዝ የሚያስችል የፓርላማ መቀመጫ ብዛት | ከግማሽ በላይ | ከ2/3 በላይ | |
| 11 | የምርጫ ሕጉ የተሻሻለበት ዘመን (ዓ.ም) | ? | 1994 | |
| 12 | የምርጫ ቦርዱ የተለወጠበት ዘመን (ዓ.ም) | ? | 1994 | |
| 13 | የብሔራዊ ፓርላማ መቀመጫዎች ብዛት | 546 | 123 | 4.4 |
| 14 | የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች ብዛት | 1712[4] | 1621[5] | |
| 15 | የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት | 27400 | 12826 | 2.1 |
| 16 | የአገር ውስጥ ታዛቢ ድርጅቶች ብዛት | ? | 102 | |
| 17 | የዓለም-አቀፍ ታዛቢ ድርጅቶች ብዛት | (42) | 42 | 1.0 |
| 18 | የአገር ውስጥ ታዛቢ ሰዎች ብዛት<br>(ሴቶች) | (58000)<br>? | 29637<br>8892 | 2.1 |
| 19 | የዓለም-አቀፍ ታዛቢ ሰዎች ብዛት | (1156) | 1156 | 1.0 |
| 20 | የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች ብዛት | ? | 645 | |
| 21 | የዓለም-አቀፍ ጋዜጠኞች ብዛት | (323) | 323 | |
| 22 | የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ብዛት | ? | 23 | |
| 23 | 1ኛ የወጣው ፓርቲ ያገኘው ድምፅ (መቶኛ)<br>2ኛ የወጣው ፓርቲ ያገኘው ድምፅ (መቶኛ)<br>3ኛ የወጣው ፓርቲ ያገኘው ድምፅ (መቶኛ) | ?<br>?<br>? | 47.35<br>21.87<br>20.75 | |
| 24 | የብሔራዊ ምርጫ በጀት (ሚሊዮን ዶላር)<br>ለአንድ መራጭ የወጣ አማካይ ወጪ (ዶላር) | ?<br>0.12 | 12.5<br>1.98 | <br>17 |
| | | | | |

[4] የ1992 ዓ.ም የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች (ሶማሌን ሳይጨምር) 1712 ነበር።

[5] የካምቦዲያን በተመለከተ 1621 የሚያመለክተው የኮሚዮኖችን ብዛት ነው።

## ሰንጠረዥ 2: የምርጫ ክልልና የጣቢያ ብዛት

| ክልል (አስተዳደር) | የሕዝብ ብዛት* (1996 ዓ.ም) | የምርጫ ክልል ብዛት | የጣቢያ ብዛት | በምርጫ ክልል አማካይ የሕዝብ ብዛት | በጣቢያ አማካይ የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| 1. ኦሮሚያ | 24,663,000 | 178 | 10,636 | 139,000 | 2,320 |
| 2. አማራ | 17,941,000 | 138 | 6,208 | 130,000 | 2,890 |
| 3. ደቡብ | 13,822,000 | 123 | 5,472 | 112,000 | 2,530 |
| 4. ትግራይ | 4,068,000 | 37 | 1,226 | 110,000 | 3,320 |
| 5. ሶማሌ | 4,068,000 | 23 | *1,318 | 177,000 | 3,090 |
| 6. አፋር | 1,332,000 | 8 | 488 | 167,000 | 2,730 |
| 7. ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ | 590,300 | 9 | 563 | 66,000 | 1,050 |
| 8. ጋምቤላ | 231,400 | 3 | 223 | 77,000 | 1,040 |
| 9. ሐረሪ | 177,800 | 2 | 62 | 89,000 | 2,870 |
| 10. ድሬደዋ | 353,500 | 2 | 129 | 177,000 | 2,740 |
| 11. አዲስ አበባ | 2,753,000 | 23 | 1,075 | 120,000 | 2,560 |
| | | | | | |
| ድምር/አማካይ | 70,000,000 | 546 | 27,400 | 128,000 | 2,560 |
| | | | | | |

* በግምት የተወሰደ

*ከኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የተወሰደ*

**አንቀጽ 54: የሕዝብ ተወካቶች ምክር ቤት አባላት**

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ ሁሉ አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ::

2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ:: የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የሚታመንባቸው አናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ይሆናሉ:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

3. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ከ550 የማበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሳ ብሔረሰቦች ከ20 የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይደነገጋል::

*ከምርጫ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 111/1987 ዓ.ም) የተወሰደ*

**አንቀጽ 15: የምርጫ ክልሎች**

**2. እያንዳንዱ የምርጫ ክልል 100 ሺህ ሕዝብ የሚያቅፍ ይሆናል::**

ከኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የተወሰደ

**አንቀጽ 38: መምረጥና የመመረጥ መብት**

**1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፤**
   **ሀ) በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር፣**
   **ለ) ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሠረት የመምረጥ፣**
   **ሐ) በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፤ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሠረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት::**

ከምርጫ ሕግ (አዋጅ ቁጥር 111/1987 ዓ.ም) የተወሰደ

**አንቀጽ 38: ለዕጩነት ስለሚያበቁ መመዘኛዎች**

**1. ማንኛውም ሰው፣**
   **ሀ) ኢትዮጵያዊ የሆነ፣**
   **ለ) የሚወዳደርበትን የብሔራዊ ክልል ቋንቋ የሚያውቅ፣**

*ከኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የተወሰደ*

**አንቀጽ 102: የምርጫ ቦርድ**

**1. በፌደራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል::**

**2. የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::**

Back to UEDP Home Page